# <u>የተቃዋሚዎች ክፍታ</u>

ተሻለ ለማ ቱሬ

የቀድሞው የአሜሪካ ኘሬዚዳንት ጂሚ ካርተር ከኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ጋር ብርቱ ቁርኝት አላቸው፡፡ በቅርቡ የተካሄደውን ምርጫ በመታዘብ ረገድ ከአውሮፓ ህብረት ቀጥሎ ጉልህ ድርሻ ነበራቸው፡፡ ከ14 ዓመት በፊትም ለሶስት አስርት አመታት የተካሄደውን ጦርነት ዕልባት ለማስገኘት እሳቸው በሚመሩት የካርተር ማዕከል አማካኝነት ብዙ ደክመዋል፡፡

ድህረ -ድርግ ውድቀትም ጂሚ ካርተር በሳስካዋ ግሎባል አማካኝነት ከኢትዮጵያውያን አርሶ አደሮች ጋር ጠንካራ ትስስር አላቸው፡፡

እኚህ የቀድሞ ኘሬዚዳንት ለሰላም ባደረጉት ጥረት የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የኖቤል ሽልማት ይገባቸዋል ብሎ ሰጥቷቸዋል፡፡ ከዚህ በተቃራኒ የቀድሞውን የአሜሪካ ኘሬዚዳንት በማዋረድና በመዝለፍ የሚገለፁ ሁለት ሰዎች አሉ፡፡ አንደኛው የኤርትራው ኘሬዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ ናቸው፡፡ ጂሚ ካርተር ደርግና ሻዕቢያን ለማደራደር ባደረጉት ጥረት እጅ ሊጠመዝዙ ሞክረዋል ሲሉ ኢሳያስ ኮንነዋቸዋል፡፡ የአቶ ኢሳያስስ ይሁን ምክንያቱም ኘሬዚዳንት ኢሳያስ ከአንድ የአገር መሪ በማይጠበቅና ከአለም አቀፍ ግንኙነት ህጐች አቡጊዳ ወጥተው የአሜሪካ መንግስትን፣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን ብሎም የአለምአቀፉ ማህበረሰብን ከፍ ዝቅ በማድረግ ይታወቃሉና፡፡

ጂሚ ካርተርን በመዝለፍ ሌላው ተጠቃሹ ደግሞ የቅንጅት መሪ አቶ ኃይሉ ሻውል ናቸው፡፡ አቶ ኃይሉ የግንቦቱ ምርጫ ተካሂዶ ካርተር አዎንታዊ እማኝነታቸውን በሰጡ ማግስት «ካርተር በኛ ጉዳይ ለመናገር ምን አገባቸው?» በማለት ራሳቸውን ለትዝብት ፓርቲያቸውን ለውርዳት ዳርገዋል፡፡

አቶ ኃይሉ ይህን አስተያየት ሲሰጡ ኃላፊነት የሚሰማቸው የፖለቲካ ፖርቲ መሪ፣እንደሳቸው ህልም ደግሞ ቀጣዩ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ለመሆን ከመፈለጋቸው አንፃር አፍሬባቸዋለሁ፡፡

አቶ ኃይሉ በቅርቡ ለቢቢሲ በሰጡት መግለጫ እብሪትና ርካሽ ብሄርተኝነት ብቻ ሳይሆን ከኢሳያስ ጋር የአመለካከት አንድነት እንዳላቸው ታዝቤአለሁ፡፡ የቡድን ሳምንት የበለፀጉ አገሮች ለኢትዮጵያ የሚያደርጉትን የዕዳ ስረዛ አቶ ኃይሉም አቶ ኢሳያስም ተቃውመውታል፡፡ ልዩነቱ አቶ ኢሳያስ ኘሬዚዳንት መሆናቸውን ነው፡፡ ለነገሩ በቀይ ሽብር ዘመን በሚኒስትርነት ደረጃ ያገለገሉት አቶ ኃይሉ ቀጣዩ ጠቅላይ ሚኒስትር ለመሆን «ዘመቻ ነገደ ጉበዜ» በሠላም ወዳዱ ኢትዮጵያዊ ላይ አውጀው የለ?

አቶ ኃይሉ ከቢቢሲ ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ ስለቅንጅትና እሳቸው ያለኝ አስተሳሰብ ተለውጧል። ኢህአዴግን ባሉት ችግሮች ሳቢያ ድምፅ መንፈጌ ይቆጠኝ ጀምሯል። ሚስቴን ልጄን ባሌን አባትና እናቴን ሳይል ግንባሩን ለቀይ ሽብር የሰጠ በርካታ ኢትዮጵያዊ ባለበት አገር አቶ ኃይሉ ሻውል ልጆቻቸውን ለማሳደግ ሲሉ ሁለት አመት በደርግ ውስጥ መሥራታቸውን ደረታቸውን ነፍተው ለቢቢሲ ቴሌቭዥን ሲናገሩ ጋዜጠኛው ራሱ ሳይታዘባቸው ይቀራል? ለኔ ግን አቶ ኃይሉ ሀቀኛም ልበሙሉም አይደሉም። እንኳን አገር ድርጅት የመምራት ብቃቱ የላቸውም። ዛሬም ግን በንፁሀን ደም ስልጣን ይቋምጣሉ። ደርሰው ጀግና ነኝ ይላሉ።

ከዚህ ሌላ በጣም የሚገርመው የደርግን ከፉነት ለመመርመር ሁለት ዓመት አካበቢ የወሰደባቸው የቅንጅት ሊቀመንበር አቶ ኃይሉ ሻውል ጥሩ መሪም ፈጣን ተማሪም አይደሉም። አቶ ኃይለ ሻውል በዚህ ቃለምልልሳቸው በርካታ ለትዝብት የሚዳረጉ ነገሮች እንደተናገሩ ቴሌቭዥኑን ደግመው ሲያዩ እሳቸውንም ያስቆጨ ወደመሰለኝ ሌላ ነገር ልውሰዳችሁ።

ከምርጫው በኋላ መንግስት በቁም እስር እንዳስቀመጣቸው ሲገልፁ የከረሙት አቶ ኃይሉ ሰሞኑን በቴሌቭዥን መስኮት የሰማነው ደግሞ ብጥብጡ ሲከሰት በሹፌራቸው አማካኝነት መርካቶ በአካባቢው እንደነበሩ ነው። ይህ ነው በአንድ ራስ ሁለት ምላስ ማለት። በነገራችን ላይ እሳቸው የመርካቶውን ግንባር የባንክና እስር ቤት ሰባራ ሞክሼአቸው ዶ/ር ኃይሉ አርአያ ደግሞ የአራት ኪሎ ዩኒቨርሲቲ አካባቢ ግንባርን ዘመቻ ሲያስተባብሩ ነበር ብለን እንድንገምት ይፈቀድልናል?

አንድ ወዳጄ የአንዳንድ የአላማችን መሪዎች ብስለት፣ የመሪነት ክህሎት ሲያይ የተለመደች አባባል አላቸው «ከፍታ አለው» ይላል። እኔ ደግሞ የቢቢሲው ኢንተርቪው ዋነኛ የተቃዋሚ ፓርቲ ነኝ የሚለው ቅንጅት መሪ «ክፍታ» ፍንትው አድርጉ አሳይቶኛል። አቶ ኃይሉ «ሻውል ኮንስልታንሲ» በተባለው ድርጅታቸው አማካኝነት ጥሪ አማካሪ መሆን ይቻላሉ። አገር መምራቱ ላይ ግን የለሁበትም። ይህን ለማሳየት ሌላ ነጥብ ላክል።

የገጠር መሬትን በአገር ሽማግሌዎች ማከፋፈልና እንዲሸጥ እንዲለወጥ ማድረግ የአቶ ኃይሉ ሻውልና የሚመሩት ፓርቲያቸው አላማ እንደሆነ ተናግረዋል። እንዴት ? የሽማግሌዎች ሚና እስከምን ድረስ ? አቶ ኃይሉ ሌላ ጊዜ ሲያገኙ እንደሚያብራሩልን ተስፋ ላድርግ። ኢንቨስትመንትን ከማስፋፋት አንፃር አቶ ኃይሉ በዚህ ቃለምልልስ ያበሰሩን አንድ ነገር ቢኖር እሳቸው መሪ ሲሆኑ በርካታ የውጭ ኩባንያዎች ጓዛቸውን ጠቅልለው ወደ ኢትዮጲያ ይመጣሉ።

አቶ ኃይሉ ያሉትን ቃል በቃል ለመጥቀስ « ከበርካታዎቹ ኩባንያዎች ጋር ግንኙነት አለኝ» ቀደም ሲል የጠቀስኩት ወዳጄ የሚያሳድምመው ነገር ሲገጥመው ደግሞ ጉድ ነው! ጉድ ነው! ይላል። እኔም ደግሜዋለሁ። እኔ እስኪገባኝ ድረስ የኢንቨስትመንትን ፍሰት በወሳኝ መልኩ በመገደብ አልያም በማበረታታት ረገድ የግል ግንኙነት እዚህ ግባ የሚባል ጠቀሜታ የለውም። ታድያ ማንን የዋህ ማስጉምዠት ተፈለገ። ይህ አሁንም በኮንሰልታንሲ ደረጃ

ሊታሰብ ይቻላል፡፡ በአገር ደረጃ ግን ባለሃብትን ለመሳብ ሠላምና መረጋጋት የተሻለ ፖሊሲና ማበረታቻዎች ዋነኞቹ ናቸው፡፡

ቅንጅት እና ሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ኢህአዴግን በዘረኛነት ሲከሱት ብዙ ጊዜ ይገርመኛል፡፡ ከተቃዋሚዎች በላይ ዘረኛ የለም፡፡ ኢህአዴግ ብሄር ብሄረሰቦች ባህላቸውና ማንነታቸው ተጠብቆ በቋንቋቸው ተናግረው በሃብታቸው ወሳኝ ሆነው ኦሮሞም ኢትዮጵያዊ፣አማራም ኢትዮጵያዊ፣ትግሬም ኢትዮጵያዊ ወዘተ መሆን ይችላል በማለቱ፡፡ ተቃዋሚዎች በዘረኛነት በፈርጁትም ይህን ለማለት የሞራል ብቃት የላቸውም፡፡ ከዚህ ውጭ ኢትዮጵያዊነት የሚታሰብበት ፖለቲክዊ ገፅታ መለወጡን ቆም ብሎ ማሰብ አስፈላጊ ነው፡፡

ወደ ቀለምልልሱ ስንዘልቅ የቅንጅት መሪ አቶ ኃይሉ ሻውል በቃለምልልሱ ፓርቲያቸው በሁሉም የህብረተሰበ ክፍል የሚደገፍ መሆኑን ለማሳየት ባቀረቡት አስረጅ አዲስ አበባ ውስጥ ተክለሃይማኖት አካባቢ ሳይቀር ተመርጠናል ብለዋል፡፡ ምን ማለት ነው? ቅንጅት ተክለሃይማኖት የማይመረጥብት ምክንያት ምን ይሆን ? አቶ ኃይሉ እንደተናገሩት ኢህአዴግን ተክለሃይማኖት አካባቢ በብዛት የሚኖሩት የትግራይ ብሄር ሳይቀሩ ተቃውመውታል፡፡ ታድያ ምኑ ነው አስገራሚው ነገር የትግራይ ህዝብ ልጆቹን መርቆ ለትግል የሸኘው ለዚህ አይነት ዲሞክራሲያዊ መብት ይመስለኛል፡፡ ይልቅስ በዚህ የአቶ ኃይሉ ንግግር ውስጥ ክፉ የጉጠኛ ነት አመለካከት ተንፀባርቋል፡፡

ተቃዋማዎች ላይ ላዩን ፖለቲካን ከኢኮኖሚ ጠቀሜታ ጋር እናስተሳስራለን ቢሉም ለነሱ ፖለቲካና ደም እንዳሁም የጥላቻ ፖለቲካ አንድ ናቸው፡፡ እንደ ኢትዮጵያውያን በጋራ እንድንኖር ከተፈለገ በግልፅ ቋንቋ መናገር ይገባናል፡፡ የትግራዩ ተወላጅ የኢህአዴግ ደጋፊ ሆነ ቅንጅትን ጨምሮ የሌላውስ ማነው ደጋፊው? ይህ የዘረኝነት አባዜ ዛሬ የተጀመረ አይደለም፡፡ የተከበሩ የም/ቤት አባል የሆኑት አቶ በድሩ አደምና ኘሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም ስለትግራይ ህዝብ ያሉትን ማስታወስ በቂ ነው፡፡ የአገሬ ሰው ከሰደበኝ የነገረኝ ነውና የሚለው ሰደቡን አልደገመውም፡፡ ያለፈው በደል ሳይሻር ሌላ መጨመር ግን ወደፊት ህዝቡን መራለሁ .. ከሚል ፖለቲከኛ አይጠበቅም፡፡

ሌሎች ብዙ አብነቶችን ማንሳት በቻልም ለኔ የሰሞኑ የቢቢሲ ቃለመጠየቅ የተቃዋሚ ፖርቲዎቻችን ማንነት /እንደጓደኛዬ አባባል ከፍታ/ አሳይቶኛል፡፡ ከብስለት ይልቅ በእብሪት ተወጥረዋል፡፡